# ለእግዚአብሔር ፍቅር

"… እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ፡፡" (ኢሳ 48÷17)


God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. / E-mail – mtizazu@hotmail.com / Ph/Fax 816 – 246 - 9395


**ጥር 1995 January 2003** "ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፣ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል፡፡" (ኢሳ 54÷13)

---------- አ ዘ ጋ ጅ መ ላ ኩ ት ዕ ዛ ዙ -------------


"ለእያንዳንዱ እንደ አቅሙ÷ ለአንዱ አምስት መክሊት÷ ለአንዱ ሁለት÷ ለአንዱም አንድ ሰጠና ወደ ሌላ ሐገር…ሄደ፡፡"
(የማቴዎስ ወንጌል 25÷15)

"…ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ÷እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ…" (1ጴጥ 4÷10)

# ከሰል አምራቹ

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት÷ ዊኒስተን ቸርችል የተባሉት ታዋቂና ተወዳጅ እንግሊዛዊ መሪ ነበሩ፡፡ እርሳቸውም በጦርነቱ ክፉት የላሸቀውን የሕዝባቸውን ሞራል ለማነቃቃት÷ ከቀበሌ ወደ ቀበሌ ይዞሩ ነበር፡፡በጦር ሠፈሮች÷በየፋብሪካዎቹና በየመንግሥት መሥሪያ ቤቶቹ በመዞር የማበረታቻ ንግግር ያደርጉ ነበር፡፡ይህ በእንዲህ እያለ ከአማካሪዎቻቸው አንዱ እንዲህ ሲል መከራቸው፡፡ "ቸርችል ሆይ፡- የከሰል አምራቾችን ከፍቶአቸዋል፡፡ ጦርነቱን በመደገፍ ያደረጉት አስተዋጽኦ በቂ ስለማይመስላቸው አዝነዋል፡፡ ጋዜጠኞችም አላስታወሷቸውም፡፡ ፊት ለፊት ስለማይታዩ አልተመሰገኑም፡፡ ስለዚህ ሂደው ያጽናኑአቸው ዘንድ ይገባል ሲል ተማጸነ፡፡

በዚህ ምክንያት ቸርችል የድንጋይ ከሰል ቆፍሮ በማውጣት ሌትና ቀን የሚለፉትን ሠራተኞች ለመጎብኘት ሄዱ፡፡ ፊታቸው እንደ ከሰሉ የጠቆረ÷ ልብሳቸው ያለ ልክ ያደፈና ላብ ያሰመጣቸው ታታሪ ሠራተኞች ተሰበሰቡ፡፡ ከዚህ በፊት እንዲህ የከበረ ባለ ሥልጣን ጎብኝቶአቸው ስስማያውቅ በመገረም ይጠባበቁ ነበር፡፡

ቸርችልም ንግግራቸውን ለመጀመር ሳይቸኩሉ፡-ሠራተኞቹንና ሁኔታቸውን ልብ አደርገው አጤኑ፡፡ ከዚያም የማይረሳውን ንግግራቸውን እንዲህ በማለት ጀመሩ፡፡ "ድሉ የእኛ ነው! ነፃነታችንን እናስከብራለን! ይህም ክፉ ጊዜ አልፎ÷ሠላም ሲሰፍን÷ ልጆቻችሁና የልጅ ልጆቻችሁ፡- "ያንን ታላቅ ጦርነት እንዴት አሸነፋችሁ?" ብለው ይጠይቋችኋል፡፡ በዚያን ጊዜ አንዱ፡- "ከሰባተኛው ብሪጌድ ጎን ተሰልፌ ተዋጋሁ" ይላል፡፡ ሌላውም "ወታደሩንና ትጥቁን ያመላለሰውን መርከብ የመራሁት እኔ ነበርሁ" ይላል፡፡ ሌላው ደግሞ "ቁስለኞቹን አክም ነበር" ይላል፡፡ ሌላም÷"የጦር መሣሪያ አመርት ነበር" ይላል፡፡ ከዚያም ንግግራቸውን ቆም አደረጉ፡፡ ሠራተኞቹም "ምን ሊሉ ይሆን ዝም ያሉት?"እያሉ ተገረሙ፡፡ ከዚያም ቸርችል ንግግራቸውን ቀጠሉና፡- ጮክ ብለው፡- እናንተ ደግሞ በሙሉ መብትና ሥልጣን፡- ሠራዊቱንና መሣሪያውን ያመላልሱ የነበሩትን መርከቦች ነዳጅ ከሰል አመርት ነበር" ትላላችሁ፡፡ ከሰል አምራች ወገኖቼ ለነፃነታችን ስላደረጋችሁት አስተዋፅኦ አመሰግናችኋለሁ፡ በማለት ንግግራቸውን ፈፀሙ፡፡

በዚያን ወቅት የጦር መርከቦች በድንጋይ ከሰል ነበር የሚንቀሳቀሱት፡፡ ስለዚህ ድል ለመቀዳጀት የከሰሉ አስፈላጊነት ከጦር መሣሪያና ከሠራዊቱ አስፈላጊነት አያንስም፡፡ ምንም እንኳን በድል ወቅት ሹመትና ሽልማት የሚሰጠው ፊት ለፊት ተሰልፈው ላዋጉትና ለተዋጉት ቢሆንም÷ ድል ለመቀዳጀት የብዙ ሰዎችን በየችሎታቸው መሰለፍ ይጠይቃል፡፡ በየትኛውም ሐገር የተገኙት ድሎች ቢመረመሩ ይህ አባባል ዕውነት ነው፡፡ ስለዚህ ቸርችል ስለ ከሰል አምራቾች የተናገሩት በማስተዋል ነበረ፡፡

-----------------------------------

የአንድን ሐገር ጦርነት ማሸነፍና አለማሸነፍ ከክርስትና ሕይወት ጋር ምን ያገናኘዋል?ይባል ይሆናል፡፡ በእርግጥ ይገናኛሉ፡፡ አንድ ሐገር ሕልውናውን ጠብቆ÷ዜጋዎቹን ተንከባክቦና በልጽጎ ነፃነቱን ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ ምን ያስፈልገዋል? የገበሬውን ማረስ÷የነጋዴውን መነገድ÷ የአንጥረኛው÷ የአስተማሪው÷ የሠራዊቱ÷ የቤተ ዕምነቱና የክነቱ ሙያተኞች ወዘተ በየሙያቸው መሳተፍ ነው፡፡ የሕብረተ ሰቡ በሙላት መሳተፍ ለሐገር ነፃነትና ብልጽግና ወሳኝ መሆኑ ይታወቀ ነው፡፡

የእግዚአብሔርም መንግሥት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ÷ለምዕመናን ተከፋፍለው በታደሉ የጸጋ ስጦታዎች (መክሊቶች) በሕብረት የሚሠራ ነው፡፡ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ከእርሻ ሥራ ጋር አመሳስሎ ማስተማሩ ይህን ያሳያል፡፡ ለምሳሌ በማቴዎስ ወንጌል 9÷37 "መከሩ ብዙ ነው÷ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፡ እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት…" ሲል በማቴዎስ ወንጌል 20 ደግሞ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ሲያብራራ "መንግሥተ ሰማያት ለወይኑ አትክልት ሠራተኞችን ሊቀጥር ማልዶ የወጣ ባለቤት ሰውን ትመስላለችና፡፡" በማለት ነው÷ የሚጀምረው፡፡

የመልክታችን ትኩረት የሆነው ከማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 25 የጠቀስነው ክፍል እንደሚያመለክተው÷መንግሥተ ሰማይ የግብርናውን ብቻ ሳይሆን የንግዱንም ሥራ እንደሚመስል ነው፡፡

. (ምዕራፉን በሙሉ አንብቡት፡፡)

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አምኖ በመቀበል ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ፡- "ለእያንዳንዱ እንደ አቅሙ÷ ለአንዱ አምስት መክሊት÷ለአንዱ ሁለት÷ ለአንዱም አንድ…" ተሰጥቶታል፡፡ ለአንተም÷ ለአንቺም፡፡ እግዚአብሔር ይመስገን፡፡ ምክንያቱም ቃሉ "እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤" በማለት፡- ለአገልግሎት እንጂ ለተመልካችነት የተጠራ ክርስቲያን አለመኖሩን ያመለክታል፡፡

የአገልግሎት ስጦታዎችን አስመልክቶ መጽሐፍ እንዲህ ይላል፡፡"እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን አንዳዶቹን÷ አስቀድሞ ሐዋሪያትን÷ሁለተኛም ነቢያትን÷ ሦስተኛም አስተማሪዎችን ÷ ቀጥሎም ተዓምራት ማድረግን÷ ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ÷ እርዳታንም÷አገዛዝንም÷ ልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችንም አድርጎአል፡፡" ይላል፡፡ (1ኛ ቆሮንቶስ 12÷28) እነዚህ መንፈሳዊ ስጦታዎች በኃይል በሚሠሩባቸው ቤተ ክርስቲያኖች ደግሞ ብንምለከት ሌላ ነገር ማስተዋል ይቻላል፡፡ ቤተ ክርስቲያኑ ፀድቶ÷ መቀመጫዎቹ በሥርዓት ተደራጅተው÷ አዲስና ነባር መዝሙሮች ተቀነባብረውና ተዘጋጅተው÷ የጽሕፈት ሥራው በአግባብ ተሠርቶ÷የሂሳብ መዝገቡ ተጠናቅቆ መያዝ ወ ዘተ፡- ይታያለል፡፡ እነዚህም ሁሉ ስጦታ ባላቸው ሰዎች ይሠራሉ፡፡ ለምሳሌ፡- የቤተ ክርስቲያንን ጽዳት በታማኝነት ጠብቆ መሥራት ከማንኛውም የጌታ ሥራ ያላነሰ ኃላፊነት መሆኑን እናስተውላለን? የእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት ሁሉም ተደምሮ የሚያስገኘው የእግዚአብሔርን ክብር ስለሆነ ሁሉም ክቡር ናቸው፡፡ ምስጋናውም በጌታ ፊት ክቡር ነው፡፡ በተሰጠው ጸጋ መጠን ለእግዚአብሔር ቤት ውበት ያገለገለ ሁሉ በመጨረሻው ሽልማቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ለስሙ ያደረግነውን ይረሳ ዘንድ ጌታ አመጸኛ አይደለምና፡፡ ጌታ ይመስገን፡፡

ነገር ግን ወገኖቼ ሆይ፡- እያንዳንዳችን የተቀበልነውን የጸጋ ስጦታ ብናውቅ እንዴት መልካም ነው? አማኝ ሁሉ የጸጋ ስጦታውን ለማወቅ ቢተጋና ቢያገኝ÷ ከመንፈሳዊ ሥራ ፈትነትና ድንዛዜ ይድናል፡፡ ጸጋ ልዩ ልዩ ነው፡፡ ለሁለት ወንጌላውያን የተሰጠ የወንጌላዊነት ጸጋ እንኳን በሁለቱ ሰዎች ውስጥ ሲሠራ÷ ከሰዎቹ ባሕሪይ ልዩነት የተነሣ ልዩ ነው፡፡ ስለዚህ የአንዱ ጸጋ ሌላኛውን ሊያስፈራው ወይም ሊጎዳው ፈጽሞ አይችልም፡፡ ይልቁንም የሁሉም ጸጋ ተገልጦ በሥራ ላይ መዋል፡-በአንድ ሐገር የሚገኙትን ማዕድኖች ሁሉ አውጥቶ ለሐገሪቱ ብልጽግና እንደ ማዋል ያለ መልካም ነገር ስለ ሆነ÷በጉጉት መጠበ ቅ አለበት፡፡ ይህም በአጸፋው ቤተ ክርስቲያንን በሰላምና በፍሬ ይሞላል፡፡

ዊኒስተን ቸርችል ለከሰል አምራቾች እንደተናገሩት፡- ውግያው ሲያበቃ መጠየየቅ ይኖራል፡፡የእግዚአብሔርም መንግሥት በሴይጣን መንግሥት ላይ ድልን ሲቀዳጅ በነጩ ዙፋን ፊት÷የምንጠየቀው ነገር ይኖራል፡፡ በዚያን ጊዜ ሁሉም እንደ ሥራው መጠን ዋጋውን ከንጉሡ ዘንድ ይቀበላል፡፡ በዚያም ጊዜ ሐዋሪያነት የተሰጠው÷ ቤተ ክርስቲያኑን ባለ ማጽዳቱ አይወቀስም፡፡ አስተማሪውም ትንቢት ባለመናገሩ አይነቀፍም፡፡ ነገር ግን፡- የተሰጠውን መክሊት ቀብሮ እንዳቆየው ባርያ ለአስፈሪ ወቀሳ መጋለጥ እንዳይሆን÷ ከአሁኑ ማሰብ አስተዋይነት ነው፡፡ የዚህም መልዕክት ዓላማ ይኸው ነው፡፡

ከዚህም ጋር መጠቀስ የሚገባው ሌላው ነገር በቃሉ ዕውቀት ለማደግ በቂ ጥረት አለማድረጋችን ነው፡፡ጌታን የተቀበለ ሁሉ ለአገልግሎት መጠራቱን የማናውቅ ብንሆን ቃሉን ባለማጥናታችን ነው፡፡ ወደ ጌታ የመጣ ሰው በስንፍናው÷ በቃሉ የሚያሳድግ ባለመገኘቱና በሴይጣን ተንኮል፡- ዕድገቱ ሊሰናከል ይችላል፡፡ይህም ብዙ አማኞች በወቅቱ አድገው ለሥራ መሰማራት ሲገባቸው÷ የተጭበረበረ የአገልግሎት ግንዛቤ ያላቸውን ሥራ ፈት ምዕመናን ቁጥር አብዝቷል፡፡

*"…እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤"*

ወገኔ፡- የተቀበልኸው የጸጋ ስጦታ ምን ይሆን? በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ በምን ሥራ ነው የምትሳተፈው?

ጌታ እስኪመጣ ወይም ወደ እርሱ እስክሄድ ድረስ÷እግዚአብሔርን በዚህ አገለግላለሁ የምትለው ድርሻ አለህ? ከሌለህ አስብበት፡ ጸልይበት:: መጋቢህን አማክርበት:: መጽሐፍን በጸሎት መርምርበት:: ያለፈው አልፎአል:: ዛሬ ግን ጌታ የሚያሳስብህ:- ተነሥተህ ፍሬአማ እንድትሆን ነው:: የሥራ ጊዜ ገና አልተዘጋምና አሁን ተነሣ!! ጌታም ያከናውንልሃል::

ስጦታህ ሐዋሪያነት÷ነቢይነት÷አስተማሪነት ወዘተ ወይም የቤተ ክርስቲያንህን ጽዳት መጠበቅ ቢሆን ልዩነት የለውም:: ሁሉም ለአንዱ ጌታ ኢየሱስ ክብርና መንግሥቱን ለመገንባት ነው:: ዋናው የድል ዋንጫችን አንድ ነው:: እርሱም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶ መንገሥ ነው::

አገልግሎት በራስ አይመረጥም:: የራስ ምርጫ ያስጨንቃል:: ነገር ግን በስጦታ ይቀበሉታል:: የመክሊት ብዛት ይለያያል:: አንዱ አንድ÷ ሌላው አምስት ሊኖረው ይችላል:: ምንም የሌለው ሥራ አጥ ግን በእግዚአብሔር መንግሥት የለም፤ እግዚአብሔር ይመስገን:: *በልዩ ልዩ ምክንያት ሥራ ፈትቶ የተቀመጠው ግን ስንቱ ይሆን?* የተሰጠህን ጸጋ ካልተረዳህ ፀሎትህ ይሁን:: ጌታ በወቅቱ ይገልጽልሃል:: ጌታ ይመስገን::

---

በዚህ ደብዳቤ ተባርከው ያውቃሉ? መልክታችን ለፀሎት ወይም ለስብከት አነቃቅቶዎት ያውቃል? ከሆነስ ለመሪዎች÷መሪም ከሆኑ ለምዕመናን አስተዋውቀው ያውቃሉ? ይህ ደብዳቤ በአካባቢዎ ቢዳረስ ሊጠቅም አይችልም? ጌታ በሚያሳይዎት ሁሉ ይተባበሩን:: ጌታ ይባርክዎ::

# የአንድ ሰው ልምምድ

አንድ ሰው ስለ ፀሎቱና እግዚአብሔር ምን እንደ መለሰለት እንዲህ እያለ ይመሰክር (ያወጋ) ነበር::

* በፀሎቴ ጌታ ብልሹ አመሌን እንዲያስወግድልኝ ለመንሁ::-------------------

ጌታም እምቢ አለኝ:: አመልህን መተው ያንተ ፈንታ ነው::እኔ ግን ለመታረም ቆርጠህ ስትነሣ በጥረትህ አበረታሃለሁ አለኝ::

ከዚያም ትዕግሥት እንዲሰጠኝ ለመንሁት፡

እርሱም እምቢ አለኝ:: ትዕግስት የመከራ ውጤት ስለ ሆነ ይታደግበታል እንጂ በስጦታ አይቀበሉትም አለኝ::

እንግዲያውስ ጌታ ሆይ ደስታ ስጠኝና ይበቃኛል አልሁት:: -------------------

እርሱም እምቢ አለኝ:: የእግዚአብሔር ፈንታ መባረክ ነው:: በረከቱን አስተውሎ መደሰት ግን የሰው ፈንታ ነው አለኝ::

የሚመቸኝን መልስ ሳላገኝ እንዳላርፍ ወስኜአለሁና:-እባክህን ጌታዬ ችግር ከሚባል ነገር አድነኝ አልሁት:: ----------------

ጌታም አይሆንም አለኝ:: ችግር በጸሎት የሚያሳድግ ÷ ከዓለማዊነት እየለየ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ ስለ ሆነ ከችግር ሁሉ ነፃ መሆን ለሰው መልካም አይደለም ሲል መለሰልኝ::

እኔም የተሻለ ፀሎት ልፀልይ አልሁና:- እባክህ ጌታ ሆይ መንፈሳዊ ዕድገት ስጠኝ አልሁት:: --------------------------

እርሱም እንዲህ አይደለም አለኝ:: የተሰጠህ ሕይወት፡ ሕያው ስለ ሆነ ታዳጊ ነው:: ቃሌን በትጋት እየተመገብህ÷ በጾምና በፀሎት እየበረታህ ማደግ ያንተ ፈንታ ነው:: እኔ ግን ማደግህን ካየሁ:- ብዙ ፍሬ እንድታፈራ አጠራሃለሁ (prune) አለኝ::

ከዚያም እግዚአብሔር ሆይ በሕይወቴ ዘመን የረካሁ እንድሆን ሁሉን ነገር ብትሰጠኝ ምን አለበት አልሁት:: -------------

እርሱም አይሆንም አለኝ:: በነገር ሁሉ እንድትረካ ሕይወትን ሰጥቼሃለሁ:: ሰው ሁሉንም ነገር ቢኖረው በሕይወቱ አይረካም፤ የተሰጠውን ሕይወት ታላቅነት ቢረዳ ግን በሁሉ ነገር የረካ ይሆናል አለኝ::

እኔም በመጨረሻው እየተሸነፈኩ መጣሁና፡ እንግድያውስ ጌታ ሆይ ሰው እንድወድ ርዳኝ አልሁት:: ---------------------

እርሱም ተባረክ ልጄ÷አሁን ገና ደረስህበት አንተ ብቻ "ባለንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ" እንጂ:- በዚህስ እረዳሃለሁ:: የሰው ልጆች ታላቁ ችግር የፍቅር እጦት ስለ ሆነ ልብህን ለፍቅር ብታነሣሣ እረዳሃለሁ አለኝ::

ከዚያም ነገሩ ትንሽ ገረመኝና ጌታ ሆይ ከእነዚህ ሁሉ ፀሎቶቼ ስለ ፍቅር የለመንሁህን መውደድህ ምክንያቱ ምንድን ነው? ብዬ ጠየቅሁት:: --------------------

ከዚያም የተጻፈውን ቃሉን ወደ ልቤ ያመጣ ጀመረ:: ቃሉም *"በሰዎችና በመላዕክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮህ ናስ ወይም እንደሚንሸዋሸዋ ጸናጽል ሆኜአለሁ::* ትንቢትም ቢኖረኝ÷ሚስጢርንም ሁሉና ዕውቀትን ሁሉ ባውቅ÷ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ ዕምነት ሁሉ ቢኖረኝ፡ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ:: ድሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል÷ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ፡ ፍቅር ግን ከሌለኝ፡ ምንም አይጠቅመኝም::" "እንዲህም ከሆነ ዕምነት፡ ተስፋ፡ ፍቅር ፡ እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፤*ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው::"* የሚለው ነው:: (1ቆሮ 13÷1-3 እና 13)



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ሲል በመስቀል ላይ በተሰዋበት ጊዜ ሬሳው ለሦስት ቀን የነበረበት መቃብር ይህ ነው:: The Garden Tomb ዘ ጋርደን ቱም የሚባለው ይህ ሥፍራ በኢየሩሳሌም ከተማ ሰሜናዊ ክፍል ይገኛል::

# ሁለቱ ልጆች

"...አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት:: ከእነርሱም ወደ አንደኛው ቀርቦ:- "ልጄ ሆይ! ዛሬ ወደ ወይን አትክልቴ ሄደህ እንድትሠራ ይሁን"አለው:: ልጁም "እምቢ አልሄድም" አለ:: ይሁን እንጂ በኋላ ተጸጸተና ሊሠራ ሄደ:: አባትየው ወደ ሁለተኛው ልጁ ደግሞ ሄደና እርሱንም እንዲሁ እንዲሠራ አዘዘው፤ ልጁም "እሺ አባቴ እሄዳለሁ"አለ:: ነገር ግን ወደ ሥራ አልሄደም:: እንግዲህ ከእነዚህ ከሁለቱ የአባቱን ፈቃድ የፈጸመው የትኛው ነው? እነርሱም "የመጀመሪያው ነዋ!" አሉ:: ኢየሱስም እንዲህ አላቸው÷እውነት እላችኋለሁ፤ኃጢአተኞችና ዘማውያን ወደ መንግሥተ ሰማይ በመግባት ይቀድሟችኋል::ምክንያቱም አጥማቂው ዮሐንስ የጽድቅን መንገድ ሊያሳያችሁ ቢመጣ አላመናችሁትም፤ኃጢአተኞችና ዘማውያን ግን አመኑት፤ይህንንም አይታችሁ እንኳ ንስሐ ገብታችሁ አላመናችሁትም::"(የማቴስ ወንጌል 21÷28-31 አዲሱ ትርጉም)

ይህ ታሪክ ክርስቲያን ነኝ የምንለውን ሰዎች ያሳስበኛል:: ቤተክርስቲያን መሄድ እንሄዳለን:: ክርስቲያን መባሉንም እንወዳለን:: የኃይማኖት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ይክዳሉ ተብሎ እንደ ተጻፈው መሆኑ ነው:: "ስሙን እሽ መገዛቱን ግን እምቢ::" እኔ ዳግመኛ ከመወለዴ በፊት ክርስቲያን ነኝ ማለቴን ትቼ አላውቅም ነበር:: በዕውነቱ ግን አመጻኛ ከሃዲ ነበርሁ:: የጌታን ማዳን አምኜ ከተቀበልሁና ከበራልኝ በኋላ ነው፡ከጣኦት አምላኪዎች እኩል ሲኦል ይጠብቀኝ እንደ ነበረ ከቃሉ የተረዳሁት:: ክርስቲያን ነኝ ልበል እንጂ ክርስቶስን በዕውነት አላወቅሁትም:: ማዳኑን በዕምነት ስላልተቀበልሁ ቃሉን ባነብ እንኳን አይገባኝም ነበር:: እግዚአብሔር ረድቶኝ ልጁን ባይገልጽልኝ ኖሮ መመለሻ ወደ ሌለው ወደ ዘላለም እሳት በሄድሁ ነበር:: ነገር ግን አንድ ቀን የኢየሱስን ማዳን ተቀበልና ዳን ብለው ሲሰብኩኝ:-ኩራቴን ጥዬ÷ተንበርክኬ÷ ተቀበልሁ:: ከዚያም በቤቴ የነበረውን መጽሐፍ ቅዱስ ገልጬ ማንበብ ስጀምር÷ ድንቅ ነገር ሆነ:: ቃሉ ይገባኝ ጀመረ:: እግዚአብሔርም ለልቤ መናገር ጀመረ:: ምንም እንኳን አዲስ አማኝ ብሆንም በጉሆኜ አለሁና፡ ድምጹን ስሰማ አወቅሁት:: በማይወሰድብኝ የየሱስ ፍቅር ተሞላሁ:: ሕይወቴንም አቃናልኝ:- ስለዚህም በሥጋና በነፍስ የባከነውን ዘመኔን ረስቼዋለሁ:: ዛሬ ለማንም የማይቀረው ሞት ቢመጣ አልሰጋም:: የዘላለም ዕረፍት በጌታዬ በየሱስ ክርስቶስ ተዘጋጅቶልኛል:: እግዚአብሔር ይመስገን:: * አንተስ? *

---

"*የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ" (1ዮሐ 5÷13)*

---

*"መዳን በሌላ በማንም የለም፡ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና::" (የሐዋ ሥራ 4÷12)*

---

***የንስሐ ፀሎት:-*** *ጌታ ኢየሱስ ሆይ! ሰለ ሰው ልጅ መሞትህን ባምንም በትምሕትህ መሠረት ባለመኖሬ ይቅር በለኝ:: ከዛሬ ጀምሮ ለትምሕርትህ አገዛለሁ:: መጽሐፍ ቅዱሴን በማጥናት ክርስትናዬን በዕውነት እከተላለሁ:: ወደ መንግሥትህ እንድትቀበለኝ:- በዕለት ኑሮዬ አንተን በመፍራት እመላለሳለሁ:: ጌታዬ ተቀበለኝ:: አሜን::*

---

ይህን ፀሎት በዕምነት ከፀለይህና ጥያቄ ቢኖርህ በዚህ ደብዳቤ መግቢያ ላይ ካሉት አድራሻዎች (ስልክ÷ፋክስ÷ ደብዳቤ ወይም ኢ-ደብዳቤ) ጻፍልን:: መጽሐፍ ቅዱስ ለምትፈልጉ ማቅረብ እንችላለን::

● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ●

"ለሁሉ ዘመን አለው÷ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው:: ለመወለድ ጊዜ አለው÷ለመሞትም ጊዜ አለው፤ለመትከል ጊዜ አለው÷ የተተከለውንም ለመንቀል ጊዜ አለው..." (መ/ መክብብ 3÷1-2)

ወደ እግዚአብሔር ፈቃድ በበለጠ የምንቀርብበትና ብዙ ፍሬ በማፍራት እርሱን የምናስከብርበት ጊዜ አሁን ነው:: በአዲስ ዓመት አዲስ ጸጋ÷ ጌታን ተስፋ ለምታደርጉ ሁሉ ይሁን፡አሜን::

**ኢየሱስ ጌታ ነው።**

**ጌታ ይባርክህ።**